# ይድረስ ለውድ እናቴ

አሰራደው (ከፈረንሳይ)

ውድ እናቴ !
ቀደምት የተባረኩ ልጆችሽ ያንቺ የእናታችንን ድንበር በአጥንታቸው አጥረው፤ ነፃነትሽን አስከብረውና ጠላት አሳፍረው አልፈዋል፤ ታዲያ ለዚህ ውለታቸው ካንቺ የእናትነት ፍቅር ሌላ የጠየቁት ልዩ ውለታ አልነበረም ፡፡
ዛሬ እኔ ልጅሽ ደግሞ ለወገናቸው ፍትህ፤ ዕድገት፤ ሠላምና እኩልነት ሲሉ በትግል በወደቁ ወንድሞቼና እህቶቼ ደም እያጠቀሰኩ ይችን ደብዳቤ እጽፍልሽ ዘንድ ፍቀጅልኝ፡፡

ውድ እናቴ !
ያለ እድሜሽ የገረጣው ዞማ ፀጉርሽ እጅግ አስረጅቶሻል፤ በሃዘን የታጠረው ሰውነትሽ ሃውልት አስመስሎሻል፤ ከዓይኖችሽ ኩሬ የሚፈልቀው እንባ ፊትሽን ሸርሽሮ ንቅሳትሽን አደብዝዞታል፤ ከአንደበትሽ ይፈልቁ የነበሩት የእናትነት የፍቅር ቃላት ከጉሮሮሽ መድረቅ የተነሳ ዛሬ አይሰሙም፤ ዘወትር ትመግቢን የነበረው ፈገግታሽ ዛሬ የእህል ያህል ናፍቆናል፤ በዞማው ፀጉርሽ ዙሪያ ሸብ ታደርጊው የነበረ ሰንደቅ አላማሽ ዛሬ ቀለሙ ከመደብዘዙ የተነሳ ንፋስ እንኳን ንቆት ከፍ ብሎ አይውለበለብም፤ ከሩቅ ያብረቀርቅ የነበረው የአንገትሽ መስቀል ማተብሽ በመበጠሱ አንገትሽ እራቁቱን ቀርቷል፤ በፍቅር ጠብተን ያደግናቸው ጡቶችሽ በደረትሽ ላይ ቁልቁል ተዘቅዝቀው የሃዘን እንባ ያነባሉ፤ የጎድን አጥንቶችሽ ለማገዶ የቀረበ እንጨት ይመስል ደርቀዋል፤ አንጀትሽ እህል ለማስተናገድ እርም ያለ ይመስል ከጀርባሽ ጋር በሙጫ ተጣብቋል፤ ፈራ ተባ እያልሽ የምታፈራርቂያቸው ከሲታ እግሮችሽን ስመለከት አጠገብሽ ሆኜ ምርኩዝሽ ባለመሆኔ ሃዘኔ እጥፍ ድርብ ሆኗል ፡፡

እናም እናት ዓለም !
በኛ በልጆችሽ ጥፋት የተነሳ መከራሽ ተከምሮ የማያልቅ ክምር ሆነ ፡፡ ሃቀኛ ልጆችሽ የኑሮ ቋት አልሞላ ብሏቸው ሸርክት ኖሮ እንደኖሩ፤ ያንቺን ሕመም ለማከም፤ ያንቺን እንባ ከአይኖችሽ ለማበስ፤ ስቃይሽ ስቃያቸው፤ መከራሽ መከራቸው፤ እንደሆነ ኑሮን ሳይኖሩት ኑሮ ኖሮባቸው አልፈዋል ፡፡ አሁንም የነሱን ፈለግ የተከተሉ ልጆችሽ ዘረኝነትን እንቢ በማለት ያንቺ የእናታችንን ማተብ ከአንገታቸው ላለማውለቅ ላንቺና ለልጆችሽ ቃል ኪዳን በመግባት አምባ ገነንነት፤ እስር፤ ግድያ፤ አድልዎ፤ ንቀዘት፤ ርሃብና በሽታ ይወገዱ ዘንድ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጆሮ ያለው ሁሉ ይሰማ ዘንድ የልጆችሽን ጩኸት ይጮሃሉ፡፡

*ዘመን ያመጣው ጉድ ሆነና: ትናንት ጨማ ይቆረጥበት፤ ጠጅ ይንቆረቆርበት፤ ጥሩ በጣም ጥሩ ጠላ፤ የራስ ቅል በሚያክል ሸክና ይጠጣበት የነበረው፤ ብሉልኝ ይኸ ለማን ይትረፍ? ይባልበት የነበረው የልጆችሽ ቤት: ዛሬ የእህል ሽታ ናፍቆታል ::*

*ጥሩ የማር ጠጅ በተንቆረቆረበት ጉሮሮ: ዛሬ ድፍርስ ውሃ እንኳን ብርቅ ሆኖበታል፤ ትናንት ሽጋ በጣም ሽጋ የዶሮ ወጥ ይንተከተክበት የነበረው ቤት፤ ዛሬ ያልፈላ ሽሮ ሽታውን ነፍጎታል:: ትናንት ማሙሽና ማሚት በደስታ ይቦርቁበት የነበረው ቤት፤ ዛሬ በማሙሽና በማሚት ለቅሶ ደምቋል:: ትናንት በከብት ብዛት ይጨናነቅ የነበረው የልጆችሽ በረት፤ ዛሬ የከብት ዕበት እንኳን ብርቅ ሆኖበታል ::*

*ውድ እናቴ!*
*የልጆችሽን መከራና ስቃይ በመቁጠር ሃዘንሽን እጥፍ ድርብ ላለማድረግ ስል የችግር ዝርዝሩን በዚሁ መግታት መረጥኩ::*
*የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ፤ እነዚህ የታሪክ ጉዶች ዓይናቸው ታውሮ፤ ሕሊናቸው በጥላቻ ደንድኖ፤ የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክሽን በፈረንጅ ላፒስ እየፈገፈጉ፤ የነፃነት ጥበብ ኩታሽን ቀደው፤ ቀስተደመና ሰንደቅ ዓላማሽን አዋርደው፤ የመቶ አመት የታሪክ ድሪቶ ሊያለብሱሽ የዳዳቸውን ዘንግተው፤ ዛሬ በስምሽ በመነገድ በቃኝ የማይል መቃብር ሆዳቸውን ለመሙላት በደም የተዋጀ ድንበርሽን አስደፍረው:*

***መሬት ላራሹ! መሆኑ ቀርቶ:መሬት ለድንበር ዘለል ከበርቴ!***

*እየተቸበቸበ፤ ሕዝባችን በኑሮ ውድነት ተለብልቦ ከስሎ ባረረበት፤ ወጣቱ በሥራ አጥነት፤ በአድሎና በዘረኝነት ተማሮ: በገዛ አገሩ እምነት በማጣት፤ ለስደት እየተዳረገ፤ የሕግ የበላይነት ጠፍቶ ፍትህ በሌለበት፤ የስልጣን ብልግና በሰፈነበት፤ ንቅዘት (ሙስና) ተንሰራፍቶ ተጠያቂነት በሌለበት፤ የዋልጌዎች ስርአት፤ ኢኮኖሚው አደገ ቢሉ ከራሳቸው በስተቀር የሚያታልሉት አይኖርም:: ዛሬ ባገራችን በኢትዮጵያ በተጨባጭ የሚታየው መብራት በፈረቃ፤ ውሃ በፈረቃ፤ ምግብ በፈረቃ፤ የነዳጅ፤ የመጓጓዣ፤ የዘይት፤ የስኳር.. ወዘተ ዋጋ ወገናችንን እየደቆሰው፤ የኢኮኖሚ እድገቱ ምኑ ላይ ነው? ወይስ እነሱ ጠግበው ስለበሉ ብቻ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያገሳዋል ?!*
*ቂም አርግዞ በደል የወለደ፤ ከአንድነት ይልቅ በዘር፤ በጎሳና በሃይማኖት የሚከፋፍል፤ ሕፃን፤ ሽማግሌ፤ አሮጊትና ወጣት በጅምላ የሚገድል፤ የሚገነጥል የሚያስገነጥል፤ የሕዝብ ፍቅርና ክብር የጎደለው ለስልጣኑ እንጂ ለሕዝብ ደንታ የሌለው እንዴት ይታመናል ?*

*እነዚህ ጉዶች የአስተሳሰብ አድማሳቸው ውሱን በመሆኑ፤ ትናንት ያሉትን ረስተው ዛሬ ባንቺ በናታችን ስም ሲምሉና ሲገዘቱ ሰንሰማ  እውነትም ፈጣሪ ህሊናውን ነፍጎ ሆድ ብቻ እንደፈጠረላቸው ለመረዳት በቅተናል ::*

*እናት ዓለም!*

*የልጆችሽ ማንነት መግለጫ የሆኑ ከሁለት መቶ በላይ ቋንቋዎች እያሉ፤ በጥቁር ገላቸው ላይ ነጭነት መለበጥ የናፈቃቸው ዲቃላዎች፤ ሳይማር ባስተማራቸው ድሃ ወገናቸው ላይ እንደ ኩይሳ በመኮፈስ በባዕድ ቋንቋ ኳኳታቸውን ሰንሰማ፤ ነብሳቸው ከሥጋቸው ጋር የምታደርገውን ሙግት መገመት ችለናል:: ይህ አልበቃ ብሏቸው፤ የብዙሃን ልጆችሽን የማሰብ ነፃነት በመገደብ፤ አንደበታቸውን ዘግተው በዝምታ ባሕር ውስጥ ደፍቀው ለመግደል፤ ሕዝባችን ትክክለኛ መረጃ እንዳያገኝ፤ የነፃ የመረጃ ምንጮችን ለማምከን ሌት ተቀን ይባጃሉ::*

*ውድ እናቴ!*

*ኩራትሽን፤ ታሪክሽንና የነፃነት ተምሳሌነትሽን ከቀሩት ሃቀኛ ልጆችሽ ጋር በመሆን ላንቺ ክብርና እድገት ከመጣር ይልቅ፤ ከአይዞህ ባዮቻቸው የውጭ ጠላቶችሽ የሚጣልላቸውን ፍርፋሪ በመለቃቀም አንቺን ማድማቱን መርጠዋል: እነዚህ ከሃዲ ልጆችሽ የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብለን ፈጣሪያችንን እንደማንለምን እወቂልን፤ ከአሁን በኋላ ዳግም በምድርሽ የታሪክ ሙጃ እንዳይበቅል የዘሩትን እሾህና አሜከላ ማጨዳቸው የግድ ይላልና ::*

*ውድ እናቴ!*

*ላንቺ መስዋዕትነት ለመክፈል በቆረጡ ልጆችሽ ደም፤ እንደ ጲላጦስ እጆችሽን ብቻ መለቃለቅ ሳይሆን አከላትሽን በሙሉ ታጥበሽ ትጠሪ ዘንድ ምኞታቸው ነው::*
*ያም በመሆኑ ብዙዎች ልጆችሽ ላንቺ ለእናታችን ልዕልና ተሰውተዋል፤ በዚህም ነብሳቸው በሃሴት ተሞልታ በማሕጸንሽ የሰላምን እንቅልፍ ያንቀላፋሉ::*
*የሚፈሰው የልጆችሽ እንባ የሚፈጥረው ጎርፍ፤ ግሳንግሱን ጠራርጎ ምድርሽን ካጠራ በኋላ፤ ከአድማስ ባሻገር በሚፈነጥቀው የፀሐይ ጨራ፤ የልጆችሽ ልብ በደስታ ሞቆ ይፈካል:: ወደ ፈጣሪሽ በተዘረጉት እጆችሽ እቅፍ ውስጥ ሆነው፤ በአንድላይ እጅ ለእጅ በመያያዝ፤ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመዘመር፤ ያዘቀዘቀው ሰንደቅ ዓላማሽን በተራሮችሽ ጫፍ ላይ እንደገና ከፍ አድርገው ያውለበልቡታል::*

*ድል ለሃቀኛ ልጆችሽ!!*
*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!*

*ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ.ም. (May 12/2011)*